# ከነብያዊው ስደት ከምንቀስማቸው ትምህርቶች አንዱ አገር ግንባታ ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَالَّذِينَ هَاجَرُوا وَجَاهَدُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أُولَئِكَ يَرْجُونَ رَحْمَتَ اللَّهِ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑትና እነዚያም (ከአገራቸው) የተሰደዱት በአላህም መንገድ ላይ የተጋደሉት እነዚያ የአላህን እዝነት ይከጅላሉ፡፡ አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የአላህ መልክተኛ ከመካ ኢል ሙከረማ ወደመዲና ኢል ሙነወራ ያደረጉት የሃይማኖት ስደት የሰውን ልጅ ታሪክ በከፍተኛ ደረጃ የለወጠ ታላቅ ታሪካዊ ክስተት ነበር፡፡ እኛ በአሁኑ ወቅት በህበረተሰቡ እድገትና በስልጣኔው ግንባታ ረገድ አስተዋጽኦ ያለውን የዚህን ስደት ትርጉም ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ይህ ስደት እውነትን ከከንቱ በጉልህ መልኩ የለየ ከመሆኑም ባሻገር ፍትህ፣እኩለነት፣ የእምነት ነጻነት የሰብአዊ ሙብት መከበረን መሰረት ያደረገ ሲቪላዊ ሀገር ለማዋቀር አወንታዊ ሽግግር ነበር፡፡ እንድሁም ይህ ስደት ለሰላማዊ አብሮ መኖር መጠናከርና በአንድ አገር ለሚኖሩ ሰዎች የማህበራዊ ትስስርና ለተለያዩ የጋራ ኢኮኖሚዊ አንቅስቃሴ የመሰረት ድንጋይ ነበር፡፡

ነበያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከስደታቸው በኋላ የዋቀሩት መንግስት የተላያዩ መሰረቶችና ግብአቶች የነበሩት ሲሆን በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት አንደኛው ቀድመው መስጊድ መስራታቸው ነበር፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መዲና ኢልሙነወራ እንደደረሱ ከአከናወኗቸው ነገሮች መጀመሪያው መስጊድ መገንባት ሲሆን ይህም የሆነበት ከጌታው ጋር ያለው የሰው ልጅ ግንኙነት ለማንኛውም ነገር ደህንነት ጠንካራ ዋስትና ስለሆነ ነው፡፡ ትክክለኛ እምነት አፍራሽ ሳይሆን ገንቢና አበላሽ ሳሆን አልሚ የሆነ ቅን ማንነትን ለመፍጠር ዋነኛ መሳሪያ ሲሆን ከትክክለኛው እምነት በማፈንገጡ ወይም እሱን በተሳሳተ መልኩ በመገንዘቡ መጠን የአንድ ሰው ማንነት ከቅንነት ይርቃል፡፡ እንድሁም መስጊድ በማህበረሰቡ ቋሚ መርሆችንና ጠቃሚ እሴቶችን በማስረጽና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን በማቅረብ በኩል ትምህርታዊና ማህበራዊ ተልእኮ አለው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ደግሞ የምጣኔ ሀብታዊ ግንባታ ነው፡፡ አንድ አገር ያለሱ ሊገነባና ሊቆም ያማይችል ከሆኑ የሀገር ግንባታ ምሰሶዎች አንዱ ጠንካራ የምጣኔ ሀብት ነው፡፡ ጠንካራና የተረጋጋ የምጣኔ ሀብት አንድ አገር ሀገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ግዴታውን እንዲወጣ ያስችላል፡፡ እንድሁም ለህዝቡ አኩሪ ሕወትም ዋስትና ይሆናል፡፡ የአንድ አገር ኢኮኖሚ ሲዳከም ድህነትና በሽታ ይስፋፋል፡፡ ኑሮም ይወዛገባል፡፡ አዳድስ ችግሮችም ይከሰታሉ፡፡ ስነ ምግባር ይበላሻል፡፡ ወንጀሎች ይበዛሉ፡፡ ያን ሀገር ለመጉዳት፣ ለመጣልና መጨረሻ ወደሌለው ስርአት አልባነት ለመክተት ለአደፈጡ ጠላቶች እድሎች ይመቻቻሉ፡፡

በመሆኑም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የመዲና ማህበረሰብ የልጆቹን ፍላጎት ለማሟላት፣ ራሱን ለመከላከል፣ የእስልምና ተልእኮ እንድሳካና ድህንነት እንድሰፍን የሚያስችል ጠንካራ ኢኮኖሚ ያለው ማህበረሰብ እንድሆን ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ ይህንም ጉዳይ ለማሳካት ሲባል ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለመዲና ሰዎች የተፈቀደ ትርፍና ንግድ ሥራ አድል የሚፈጥር እንድሁም ለእጅ ባለሞያዎችና ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሳታፊዎች ማእከል የሚሆን -መናኻ- የተባለን ትልቅ ገበያ አዋቀረዋል፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዐጣእ ኢብን የሳር የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ ለመዲና ገበያ እንዲኖራት ባሰቡበት ወቅት ወደ በኑ ቀይኑቃዕ ገበያ ሄደው አዩ ከዚያም ወደመዲና ገበያ ቦታ አመሩና እዚይም ሲደርሱ በግራቸው መታ መታ አደረጉና (ይህ ገበያችሁ ነው አታጥቡት፡፡) አሉ፡፡› ተላላቅ የነብያችን ባልደረቦች በተላያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ተሳትፈዋል፡፡ ይህውም በግንዘብ እርዳታና በአንሳር ወንድሞቻቸው እገዛ በዘላቂነት መኖርን ባለመፈለጋቸው ነበር፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዓብደራሕማን ኢብን ዓውፍ የሚከተለውን አውርተዋል፡ ‹በርካታ ስደተኞች ወደመዲና በመጡ ጊዜ የአላህ መልክተኛ ዓብደረሕማን ኢብን ዐውፍን ከሰዕድ ኢብን አረቢዕ ጋር ወንድም ተማማቾች እንድሆኑ አዘዙ፡፡ ሰዕድም ለዓብደረህማን እንድህ አሉ፡ ከአንሷሮች በጣም ባለጸጋው እኔ ነኝ፡፡ ገንዘቤንም ከኔና ካንተ መካከል ከሁለት እከፍለዋለሁ፡፡ ዓብደራህማንም አላህ ቤተሰብህንና ገንዘብህን ይባርክልህ ገበያቸው በየት በኩል ነው? › አሉ፡፡

ይህውም ቀለቡን፣ ልብሱን፣ መድሃኒቱንና ጦር መሳሪያውን በእጁ ያለደረገ ማህበረሰብ ነገሩን፣ ፍላጎቱን፣ ቃሉንና ክብሩን በቁጥጥሩ ሰር ሊያደርግ አይችልምና ነው፡፡ የጥንት አበው እንድህ ይላሉ፡ ‹ለፈልግህው ሰው ውለታ ዋል ከዚያም አዛዡ ትሆናለህ፡፡ ከአንድ ሰው ምንም የማትፈለግ ከሆነ አቻው ትሆናለህ፡፡ ከአንድ ሰው አንድን ነገር ከፈለግህ የሱ ምርኮኛ ትሆናለህ፡፡› የላቀው ሃይማኖታችን የላይኛው እጅ ከታችኛው እጅ የበለጠ መሆኑን አስተምሮናል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ላይኛው እጅ -የሚሰጠው- ከታችኛው እጅ -የሚቀበለው- መልካም ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሓዲስ እንድህ ይላሉ፡ (ሰጭው እጅ የላይኛው ነው፡፡ ለማኙ የታችኛው ነው፡፡)

ይህ ተግባር በማህበረሰብ፣ በድርጅቶችና በግለሰብም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ገንዘብ በማህበረሰብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ሕይወትን በማሳካት እንድሁም ብልጽግናውን እውን በማድረግ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አሕመድ ሸውቂ የተባለው የግጥም ደራሲ እንድህ በማለቱ ይደነቃል፡

ሰዎች ገሀራቸውን የሚገነቡት በእውቀትና በገንዘብ ነው፡፡ ሀገር በድንቁርናና በእጦት ሊገነባ አይችልም፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) የዚህ ዓይነቱን መርህ ገቢራዊ ለማድረግ የስርኣት ደንቦችን አስቀምጠዋል፡፡ መቻቻልና በግዥና ሽያጭ ወቅት መልካም መንፈስ መኖር አስፈላጊ መሆኑንም እንድህ በማለት አስገንዝበዋል፡ (በሚሸጥበት፣ በሚገዛበትና በሚፋረድበት ወቅት ገራገር የሆነን ሰው አላህ ምህርትን ይለግሰው፡፡) ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እውነተኛና ተማኝ እንድንሆን እንድህ በማለት አዘውናል፡ (እውነተኛና ተማኝ ነጋዴ ከነብዮች፣ ከጻዲቃንና ከሰምዓታት ጋር ነው፡፡) ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሸቀጥ ማካበትን እንድህ በማለት እርም አድርገዋል፡ (ምግብን ለአርባ ቀናት ያካበተ ነጋዴ ከአላህ ራሱን አርቋል አላህም ከሱ ርቋል፡፡) ከዚያም አልፎ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በገበያ በራሳቸው በመገኘት ግብይትን ይከታተሉና ሰዎችም ለወገን የሚጠቅሙ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይመክሩም ነበር፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ ብለዋል፡ ‹የአላህ መልተኛ አንድ ቀን በገበያ ባለ የምግብ ክምችት አለፉ፡፡ በሱም አጃቸውንም ባስገቡ ጊዜ ጣታቸው እርትበት ባለበት ክፍል ደረሰ፡፡ (አንተ ባለምግቡ ይህ መንድን ነው?) አሉት፡፡ እሱም የአላህ መልክተኛ ሆይ ዝናብ ደርሶበት ነው አለ፡፡ እሳቸውም (ሰዎች እንዲያዩት ከላይ በኩል አታደርገውም ነበርን) አሉትና (የሚያታልል ሰው ከኛ አይደለም) አሉ፡፡

ከተጠቀሱት ድንቦች ሌላው ደግሞ የመዲና ሰነድ ነበር፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከስደት በኋላ ጠንከራ አገር ለማዋቀር ባሰቡ ጊዜ የመዲና ሰነድ የተበላውን መመሪያ አስቀመጡ፡፡ ነብያችን (ሶ.አ.ወ.) ከሙሃጂሮችና አንሷሮች መካከል ወንድም ተማማችነት በመፍጠር ብቻ አልተወሰኑም፡፡ ይልቁንም በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እጅግ ታላቅ የሚባለውን የመዲናን ሰነድ ሲነድፉ የሰብኣዊ መብት፣ የማህበረሰቡ አባላት መብትና ግዴታን እንድሁም የሰላማዊ አብሮ መኖርን መሰረት በማድረጋቸው ወደአድስ የስብእነት ትርጉም ተሸጋግረዋል፡፡ በመሆኑም ሰነዱ በገራ ኑሮ ህግ ዘርፍ ታላቅ ሰነድ የሚል ስያሜን አትርፏል፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከመዲና አይሁዶችና ከሌሎችም የመዲና ነዋሪዎች ጋር በፈረሙት ውል ለነሱ በደህንነት፣ በሰላም፣ በነጻነትና በጋራ መከላከል ዘርፎች ለአይሁዶች ሃይማኖታቸው እንደተከበረ ሆኖ በደል እስካልፈጸሙ ድረስ የሙስሊሞችን ሙሉ መብት ስጥተዋቸዋል፡፡ በዚህ ሰነድ የሃይማኖት ነጻነት በግልጽ ተወስቷል፡፡ ይህም ማንኛውም ሲቪላዊ መንግስት ሙስሊሞችንና የሌላ እምነት ተከታዮችን የሚያካትት መሆኑንና በምብትም ሆና በግዴታ እኩልነታቸው የተከበረ መሆኑን ያረጋግጣል ማለት ነው፡፡ይሁንና ውል ማክበርና ከትንኮሳ መራቅ የሚለው ነጥብ የተከበረ መሆን ይኖርበታል፡፡

መላ የሰው ልጅ በሰላም አብሮ መኖር ወቅታዊ ተጨባጩ ግድ የሚያደርገው ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ግዴታ ነው፡፡ ይህም እውን ይሆን ዘንድ የአንድ ሀገር ነዋሪዎች ያለማዳላት ተመሳሳይ መብትና ግዴታ ያላቸው መሆኑ እንዲረጋገጥላቸው ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَا إِكْرَاهَ فِي الدِّينِ قَدْ تَبَيَّنَ الرُّشْدُ مِنَ الْغَيِّ. }

ትርጉሙም (በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ይህን መርህ በተጨባጭ ሙሉ በሙሉ ገቢራዊ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም አምነቱን እንድቀበል ማነንም አላስገደዱም፡፡ ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ማንኛውንም ቤተ ጸሎትን አላፈረሱም፡፡ ምክኒያቱም የእስልምና

እምነት ለእምነት ነጻነት ዋስትና ሰጥቷልና፡፡ ይህን ዓይነት የሃይማኖት ልዩነት ማነም ሊለውጠው አይችልም ምክኒያቱም የፈጣሪን ፍርድ ይጻረራልና፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَوْ شَاءَ رَبُّكَ لَآمَنَ مَنْ فِي الْأَرْضِ كُلُّهُمْ جَمِيعًا أَفَأَنْتَ تُكْرِهُ النَّاسَ حَتَّى يَكُونُوا مُؤْمِنِينَ}

ትርጉሙም (ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር፡፡ ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ታስገድዳለህን፡፡) ማለት ነው፡፡ በአንድ አገር ግንባታ የእምነት ነጻነት፣ መብትና ግዴታ መከበር ዋና ዋና መሰረቶች ናቸው፡፡ ምክኒያቱም ለህዝቡና ለማህበረሰቡ ትስስር ከፍተኛ ሚና ያለቸው በመሆኑ ነው፡፡ የአስልምና እምነት የሌላ እምነት ተከታዮችን ለነሱና ለሃይማኖታቸው የሚያስከፋ ነገር መናገርን ከልክሎናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَلَا تَسُبُّوا الَّذِينَ يَدْعُونَ مِنْ دُونِ اللَّهِ فَيَسُبُّوا اللَّهَ عَدْوًا بِغَيْرِ عِلْمٍ كَذَلِكَ زَيَّنَّا لِكُلِّ أُمَّةٍ عَمَلَهُمْ ثُمَّ إِلَى رَبِّهِمْ مَرْجِعُهُمْ فَيُنَبِّئُهُمْ بِمَا كَانُوا يَعْمَلُونَ. {

ትርጉሙም (እነዚያንም ከአላህ ሌላ የሚገዙዋቸውን (ጣዖታትን) አትስደቡ፡፡ ድንበርን በማለፍ ያለዕውቀት አላህን ይሰድባሉና፡፡ እንደዚሁ ለሕዝቦች ሁሉ ሥራቸውን ደግ አስመሰልንላቸው፡፡ ከዚያም መመለሻቸው ወደ ጌታቸው ነው፡፡ ይሠሩት የነበሩትንም ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡) ማለት ነው፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች የስነ ምግባርና መልካም ጉርብትና መንፈስ እንድኖራቸው ያዛል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{لَا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُمْ مِنْ دِيَارِكُمْ أَنْ تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ. {

ትርጉሙም (ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም ተከታዮቹ የሌላ እምነት ተከታዮችን ስሜት በውይይትና በክርክር ጊዜም እንኳ ቢሆን እንዲያከብሩ ያዛል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تُجَادِلُوا أَهْلَ الْكِتَابِ إِلَّا بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ إِلَّا الَّذِينَ ظَلَمُوا مِنْهُمْ وَقُولُوا آمَنَّا بِالَّذِي أُنْزِلَ إِلَيْنَا وَأُنْزِلَ إِلَيْكُمْ وَإِلَهُنَا وَإِلَهُكُمْ وَاحِدٌ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ. {

ትርጉሙም (የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፡፡ ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡፡ በሉም «በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን፡፡ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፡፡ እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን፡፡) ማለት ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ አንጻር ነው እንግዲህ የመዲና ሰነድ የአንድ አገር ነዋሪዎችን ትስስር እውን የሚያደርገውን፣ ስልጣኔ የሚፈጥረውንና የሰው ልጅ ጥቅም አንድከበር የሚያግዘውን የሰብአዊ ሙብትን በማክበር ረገድ ሊከተሉት የሚገባ አርአያነት ያለው ሰነድ ነው የተባለው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

***

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

አገር ከፍተኛ እሴትና ታላቅ ደረጃ ያለው መጠጊያ ነው፡፡ እሱን ማፍቀር ስለእሱ መከላከል የሰው ልጅ መንፈስ የታነጸበት ተፈጥሮ ሲሆን ሃይማኖት የሚደግፈውና የሀገር ወዳድነት ግዴታ ነው፡፡ ነብያችን በሀገር ፍቅር፣ ልባቸው በሱ በመታሰሩ አርአያነት ያለው ተግባራቸውን የመጀመሪያ አገራቸውን መካን በማናገር እንድህ በማለታቸው አረጋግጠዋል፡ (ለኔ ተወዳጅ የሆንሽ ምን ያማርሽ አገር ነሽ ሰዎችሽ ካንች ባያወጡኝ ኖሮ ባልወጣሁ ነበር፡፡)
ነብያችን ወደመዲና ተሰደው በሷም ከተረጋጉ በኋላ ይህን ሁለተኛውን አገራቸውን እንዲወዱት በሱም ሰላምና መረጋጋት እንድሰፍን አላህን እንድህ በማለት ጸሎት አድርገዋል፡ (ጌታችን ሆይ እኛ መካን እንደምነወድ ወይም ከዚያበላይ መዲና እድንወድ አድርገን፡፡) ከመንግሰትና ከሃይማኖት መካከል ያለው ግንኙነት ተጻራሪ ሳይሆን አንዱ ሌላውን የሚያሟላ ግንኙነት ነው፡፡ ሀገርን መጠበቅ መሟላታቸው ግዴታ ከሆኑ አጠቃላይ አላማዎች አንዱ ነው፡፡ ስለሀገር መከላከልና ድህንነቱን መጠበቅ ለሱም መስዋእትነት መክፈል በምድሩ የሚኖርና በሰማዩ የሚጠለል ሰው ሁሉ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው፡፡ የሀገር ፍቅር በዘተፍጥሮ ሚሰማን ስሜት ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡና ለግለሰቡም በሚጠቅሙ ነገሮች መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ሀገር ጠንካራና የተከበረ ሆኖ እንድኖር መስዋእትነት መክፈል ለሁሉም የማይቀር ተግባር ነው፡፡ እውነተኛ ሀገር ወዳድነት የምናነግበው መፍክርና የምንደጋግመው ቃል ብቻ ሳይሆን እምነት፣ ስርአትና ስጦታን ያካተተ ተግባር ነው፡፡ ሀግር ወዳድነት የሕይወት ሰርአት እንድሁም የሀገር ልብ ትርታና የተደቀነበትን ችግር የምናውቅብት ስሜትና ለሱ መስዋእትነት ምንጊዜም ዝግጁ የምንሆንለት መጠለያ

ነው፡፡ ለአላህ የገቡትን ቃል ያከበሩና ሀገራቸውን ለማስከበርና ከፍተኛ ደረጃም ለማድረስ መስዋእትነት የከፈሉ ሰዎች እንኳን ደስ ያላቸው፡፡

ጌታችን ሆይ ሐገራችንና ህዝባችንን ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን በሱም የሚቃጣን የተንኮለኞችን ተንኮል፣ የምቀኞችን ሴራና የጠንቀኞችም ደባ በነሱው ላይ መልስባቸው፡፡